# የዕውነት ስርየቱ የታሪክ ትምህርቱ 1

ከነበለት ሀብስቱ

በዚህች የውሸት ዓለማችን መድረክ ላይ ተዋናኝ የሆኑት ሁሉ ዕውነት በዕውነትነቷ ታሪክም በእንዝርቷ እንዳይሽከረከሩ የሚታገሉ ፍጥረታት ናቸው። ብዙዎቹ በሌሎች ኪሳራ ለራሳቸው የደለበ ትርፍ፣ በሌሎች ስቃይና መከራም የግላቸውን ደስታና ፍስሃ፤በሌሎችም ሞት የነርሱን የዕ ድሜ ዝንግግ የሚያስረዝሙ ነብሰ በላ ግለኞች ናቸው። ለዚህም ግብዓት ሲሉ ዕውነቱን እያወቁ እንደ ጲላጦስ ዕውነት ምንድን ነው? ብለው የሚጠይቁ ሃኬተኞች ናቸው።በዚህ መልክ የተመሰረተው ወያኔ ሃርነት ትግራይ አሁን ላለበት ደረጃ የደረሰው ያልነበረ ፅፎ እያነበበና ያልተሰራ ፈ ;ሮ እየተረጎመ የተሳሳተ ታሪክ ፈብርኮ የትግራይን ህዝብ በውሸት ሰብኮ ነበር።የዚህ ውሸት ደራሲ ከነበሩት አንዱ አረጋዊ በርሄ ነው።

ክቡራትና ክቡራን ለዚህች ፀሁፌ መንስኤ የሆነኝ የወያኔው መስራች አቶ አረጋዊ በርሄ በደም የዋጀ እጁን በይቅርታ ሳያነፃ ላገርና ለህዝብ ሲል ኢህአፓ በሆደ ሰፊነት ይህን ነብሰ ገዳይ ለዓመታት በጫንቃው አዝሎ ለተጓዘበት ወሮታ ያጎረሰውን እጅ መንከሱ ነው። አቶ አረጋዊ በርሄ የኢትዮጵያን ማጥፊያ ተጋድሎ ሃርነት ትግራይን(ተሃትን) ከመሰረቱት ፀላየ-ሰናዮች አንዱ ነበር። የስታሊንን የብሄሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ፍልስፍና መሰረት አድርጎ የተነሳው አረጋዊ በርሄ የትግራይ ህዝብ በአማራ የበላይነት እድገቱ እንደ ጫጫ፣ የዕኩልነት መብቱ እንደ ተረገጠ፣ የትምህርት እድልም እንደ ተነፈገው፣ ወዘተ አድርጎ ቀሰቀሰ። አማራውን በትግሬ ለማስጠላት ከአማራ ጋር እንኳን አብሮ መኖር አብሮ መለመን አይቻልም ሲልም የጥላቻ መርዙን ዘራ።

እናት ኢትዮጵያም እንደ አፈሯ ቀይና ጥቁር ቀለም በአንድ በኩል ኢህአፓን፣ (አባይ ኢትዮጵያን) በሌላ መልኩም በትግራይ ትግርኝ ሪፓብሊክ የተለከፉትን ጠባቦች ተሃትን አበቀለች። በተለይ የትግራይ መሬት ደደቢት ላይ ወያኔን አሲምባ ደግሞ ኢህአፓን አሳደገ። ሁለቱ ድርጅቶች በትግራይ ህዝብ ዘንድ የነበራቸው ቅቡልነት ግን የሰማይና የመሬት ያክል ልዩነት ነበረው። የትግራይ ህዝብ ለኢህአፓ የቸረው ያልተቆጠበ ፍቅር ወያኔን የባህር ላይ ኩበት አደረገው። ይህም የህዝብ አቋም በነ አረጋዊ በርሄ ዐይን ውስጥ ትልቅ ጋሬጣ አበቀለ።ስለሆነም እነ አረጋዊ በርሄ በትግራይ ምድር የበላይነትን ለመቀዳጀት ያልነበረ ታሪክ ፅፈው አነበቡ።

ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች የሚል ።ይህንንም የውሸት ታሪክ በማኒፌስቷቸው ይፋ አደረጉ።ከዚህም ጋር ተያይዞ ኢህአፓ የኤርትራን ጥየቄ የብሄር ጥያቄ እንጅ የቅኝ ግዛት፡ጥያቄ አይደለም ማለቱ ለወያኔ የሻቢያን ድጋፍ በማስገኘቱ የከባቢውን የሃይል አሰላለፍ አዛነፈው። ከዚሁ በተጨማሪ በራሱ በኢህአፓ ውስጥም ከወያኔ ጋር ለመወገን ያኮበኮቡ አንጃዎች(እነ ብርሃኑ ነጋ) ተጨምረውበት በኢህአፓ ላይ የደመና ጥላ አንዣበበ። በከተማም የፋሽሽቱ ደርግና የባንዳዎቹ ቀይ ሽብር ኢህአፓን ያዋከብ ስለነበር እነ አረጋዊ በርሄ ያን አጋጣሚ ተጠቅመው አሲምባ ላይ ጦርነት ከፈቱ። ኢህአፓ ባንድ በኩል የደርግንና የመኢሶንን በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔን ጥቃት ሲከላከል ሻቢያ ከወያኔ ጎን ተሰልፎ ሶስቱ ሃይሎች ተባብረው ኢህአፓን ከትግራይ መሬት አስወጡት። ያረጋዊ በርሄ እጅ በኢህአፓ ደም መዋጀት የጀመረው ከዚህ ጊዜ አንስቶ ነበር።

እነ አረጋዊ በርሄ በዚያን ወቅት ኢህአፓን አባይ ኢትዮጵያ፣ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩትንም የትግራይ ተወላጆች ኮራኩር አማራ በማለት ሰፊ ቅስቀሳ አካሄዱ።ኢህአፓ ግን ይህም ሁሉ ደባ እየተፈፀመበት ከወያኔ ጋር አብሮ ለመስራት ተደጋጋሚ ውይይቶችን አድርጎ ነበር።ዘጠኝ ጊዜ

በላይ ያደረጉት ውይይቶች ዘጠኙንም ወያኔን ወክሎ ያከሸፈው አረጋዊ በርሄ ነበር።

ቀጥሎምም ትግራይ ለትግራዊያን ብቻ ብሎ ጦር ሰበቀ። ቀደም ሲል የኢህአፓ አባላት ይህ እንደሚመጣ ገምተው ስለነበር ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም ተሃትን በለጋዋ እንምታት ሲሉ ዳሩ ከውሃ ደም ይፍራል የሆነባቸው እነ ዘሩ ኩህሸን ግን ይህማ እውነትም ጠባቦቹ እንደሚሉት ትምክህተኝነት ነው። ስለ ብሄሮች እኩልነት እየሰበክን የብሄር ጥያቄ አንስቶ የሚታገልን ድርጅት ማጥፋት ሂፖክራትነት ነው በማለት በኢህአሠ ሞራል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸለሱ። እነዚህ የውስጥ አርበኞች ብዙዎቻችን ባልገባን መንገድ የሠራዊቱን ወኔ ሰልበውና የንዴት ፍላሎቱን አበርደው ለነ አረጋዊ በርሄ ድንገተኛ አደጋ አመቻቹት።

አረጋዊ በርሄም ኢህአፓን በድርድር እያዘናጋ ከደርግ/ መኤሶንና ከሸዐቢያ ጋር አሲሮ ኢህአሠን ለመጨፍጨፍ መሰናዶ ያደርግ ነበር። ድንገተኝነትን ተጠቅሞ ድል የቀናው ወያኔ ኢህአሠን ከአሲምባ ብሎም ከትግራይ ማስወጣት ቻለ። የሚገርመው ነገር ግን ደርግም ከወያኔ ጎን ተሰልፎ ወሎ ውስጥ ሌላ የጦር ግንባር በኢህአሠ ላይ በመክፈቱ ነበር።ይህም ድርጊት የነ አረጋዊ በርሄን ከሸዐቢያ ጋር ስሙር ግንባር የመፍጠር ዕድል አመቻቸ።የሻቢያን ሙሉ ድጋፍ የተቸረው ወያኔም በኢህአፓ ላይ ሸንበቆችና ወልቀይት ውስጥ የተጠናከረ ጥቃት ሰነዘረ።አከታትሎም በአረ ጋዊ በርሄ አዝማችነት ወልቃይት ውስጥ ገብቶ የብዙ ህዝብ ህይዎት አጠፋ። ያ ወረራ ነበር ለዛሬው የጎንደርና የወሎ መሬት ወደ ትግራይ ክልል መቀላቀል መነሾ የሆነው።

አረጋዊ በርሄ ይህን ሁሉ ወንጀሉን እንደ ያዘና ይልቁንም በንፁሃን ደምም የወየበ እጁን በይቅርታ ሳያጥብ ነበር ፓሪስ አንድና ሁለት በሁዋላም በህብረቱ ውስጥ ከኢህአፓ ጋር እኩል ድምፅ ይዞ የተቀመጠው። በመሪነት ተሰይሞም በኢህአፓ ገንዘብና መዋቅር የኢትዮጵያ ጠበቃ እስኪመስል ድረስ ዓለምን ሲዞር ያለ መልኩ መልክ ተቸረው። በዚህ መንገድ አረጋዊ በኢህአፓ የመቻቻል ባህል ላይ ተመርኩዞ ነበር ከህጢአቱ ሳይነፃ ወደ ህዝብ አደባባይ የዘለቀው።

ቬትናሞች የአሜሪካኖችን የኢምፔሪያል ቀንበር ለመስበር በሚደረገው ግብግብ የደቡብ ወንድሞቻቸውን የትግሉ ተሳታፊ ለማድረግ ከደቡብ ዘውጌዎች ጋር ሲቀላቀሉ እነ እርሱን ለመምሰል የግድ ሁለት የታች ጥርሶቻቸውን ማውለቅ ነበረባቸው። ኢህአፓዎችም እንደ ቬትናሞች አገራቸውንና ህዝባቸውን ነፃ ለማውጣት ሲሉ የትናንት ገዳዮቻቸውን አረጋዊ በርሄንና ነገደ ጎበዜን አቅፈው ቀደም በኢድሃቅ፣ በሁዋላም ፓሪስ አንድና ሁለት፣ ቀጥለውም ህብረት ብለው ታግለዋል። ይህ የኢህአፓ የመቻቻል ባህል ግን ከሞኝ በራፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ ሆኖ አረጋዊ በርሄንና ነገደ ጎበዜን ከኢህአፓ ጀርባ ሴራ ለመጎንጎን አበቃቸው። ድሮውንም ኢድሃቅም ሆነ ህብረቱ ለነዚህ ነብሰ ገዳዮች ጊዜአዊ ዋሻ ከመሆን ያለፈ ትርጉም ስላልነበረው ዛሬ ካንጃው ከመርሻ ዮሴፍና ከሌላኛው ሳልሳዊ ወያኔ ከስዬ አብርሃ ጋር መጎዳኘታቸው የትናንቱን የመኤሶንንና የወያኔን በኢህአፓ ላይ የማሴር አድማ እድሳት አመልካች ይመስለኛል። አልገባህ ያለኝ ነገር ቢኖር የመቶ አለቃው አጃቢነት ነው። የመቶ አለቃው የጥላ ለጥላ መንገድ የጤና አይመስልም። መቶ አለቃው ልብ ብሎ ለተመለከተው አካሄዱ ሁሉ ለጆሮ ቅርበት ያለው ነው የሚመስል። ይህም ግለሰብ የሚመራው ቡድን ጭብጥ ጥሬ ይዘህ ወደ እንቅብ አሻሮ ተጠጋ እንዲሉ አራት አባላት ይዞ ነበር በኢህአፓ ጀርባ ላይ ከነ ነገደና አረጋዊ ጋር ተፈናጦ በፖለቲካው መድረክ እውቅና የተላበሰ።

ለእናት አገር ጥርስ ይሰብሩላታል እንደሚሉት ቬትናሞች ኢህአፓም ሁለት አባል ካለው ትዴት፣ አራት አባላት ካሉት ህብረ-ህዝብ፣ አምስት አባላት ካሉት መኢሶንና ሌሎች በስም ብቻ ከቆሙ ድርጅቶች ጋር በኢድሃቅ በሁዋላም በህብረቱ ውስጥ የተሰለፈው።የኢህአፓ አባላት ለእናት አገራቸው ሲሉ ነበር የአረጋዊ በርሄ ጥይት ያጎደለውን አካላቸውንና የነገደ ጎበዜ ወፌ-ይላላ ግርፋት ያለበሳቸውን ጠባሳ ለትግላቸው የጌጥ ፈርጥ አድርገው ከገዳዮቻቸውና ከገራፊዎቻቸው ጋር ህብረት የፈጠሩ። ዳሩ ወንጀለኞቹ ግን ባጎረሰ ኢህአፓን እጁን ነከሱት።

በተለይም አረጋዊ በርሄ በስልጣን ላይ ያለው የወያኔ ቡድን ሲወድቅ ሳልሳዊ ወያኔ ሆኖ ለመሰየምና የተጀመረውን የዘረኝነትና የጎጠኝነት መርህ በተያዘው የዘር የበላይነት ለማስቀጠል በሚኒልክ ቤተ መንግስት ለመሰየም ከመሰሎቹ ከነ ገብሩ አስራትና ስየ አብርሃ ጋር እንደሚወግን አንድና ሁለት የለውም። ኢትዮጵያንም ለሌላ ዙር ጥፋት እያጫት መሆኑ ለሁሉም ዜጋ ግልፅ ሊሆን ይገባል። አረጋዊ ከወያኔ ተባረርኩ ካለበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ አንድም ቀን ወያኔን በስም ጠርቶ አውግዞ አያውቅም። ይህ ሰው በስልጣን ላይ ያሉት ወያኔዎች በጨርቁ ዘር ላይ የሚያደ ርሱትን ዘረኝነት፣አድሎ፣ ግድያ፣አፈናና መረን የለቀቀ በደል በሙሉ ልብ ቢደግፍ እንጅ ይቃወማል ተብሎ አይታሰብም።

ሳልሳዊ ወያኔው አረጋዊ በርሄ በአንድ ወቅት "እይታ" ከተሰኘው መፅሄት ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ የጎንደር መሬት ወደ ትግራይ ክልል መጠቃለሉን እንዴት ታየዋለህ? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ሲመልስ ይህ ሁኔታ ወደፊት በሬፈረንደም የሚፈታ ችግር ነው ብሎ ነበር። የአረጋዊ በርሄ መልስ በራሱ የሚሰጠው ትረጉም ግልፅ ነው። የበለጠ ለማብራራት ግን የሆነውን መልሶ መቃኘት ተገቢ የሆናል። ወያኔ ሃርነት ትግራይ ወልቃይትን እንደ ተቆጣጠረ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አንድ የወልቃይት ተወላጆችን አፍሶ ወደ ትግራይ ወሰደ። ድራሻቸውንም አጠፋ። በተጨማሪም ከ1991 እስከ 1994 ባለው ጊዜ ውስጥ ሌላ ሁለት መቶ ሰባ ዘጠኝ ወጣቶችን አፍኖ ሰወረ። ከዚህ በሁዋላ የወለቃይት መሬት ባል አልባ ሴቶችን ታቅፎ ቀረ። በርካታ ህፃናትም አባት አልቦ እንዲኖሩ ለግፍ ተጋለጡ። እነዚህ እሴቶችም ለወደፊ የሬፈረንደም ድምፅ የሚሰጥ ዲቃላ እንዲፈለፍሉ የምርጥ ዘር ኮርማ ተመድቦላቸው እየተገደዱ ተደፈሩ። አረገዙ። ወለዱም። ያልፈለጉትንም ዲቃላ እንዲያሳድጉ ተገደው አሳደጉ። ዛሬ ወልቃይት ውሰጥ ዘመድ ያለው ሁሉ የእህቴ ልጅ እንጅ የወንደሜ ልጅ የሚል አይገኝም። የወያኔ ጦር ወልቃይትን ከተቆጣጠረበት ቀን ጀምሮ አስከ አሁን ድረስ በመላው ሃገሪቱ፤ በተለይም በወልቃይቶች ላይ የሚፈፀመውን በደል ሥራየ ብሎ ለዘገበው ብዙ ትልልቅ የታሪክ መደብሎች ይወጡታል።ለናሙና ያክል ግን ከዚህ ዘይን-ተረፍ የወያኔ ወንጀል አንድ ልበላችሁ።

ወቅቱ ጥቅምት 1993 ዓ.ም ነበር። ከሃያ አምስት የማይበልጡ የወያኔ ወታደሮች ወደ አንድ መንደር ጎራ ይላሉ። መንደሩ ጭር ብሏል።ለወሬ ነጋሪ የቀረ ወንድ በሰፈሩ አልነበረም። ከትንንሽ ህፃናት በቀር።ሁሉም በነቂስ ተለቅመው መደረሻቸው ከጠፋ ዝግጥግጥ ብሏል። ወታደሮቹም ይህን ሁኔታ ተጠቅመው ዘና ብለው የሚፍልጉትን ሁሉ ለማከናወን በመንደሩ ተዘዋወሩ። እየተበደኑም እንደ አፄው ዘመን ሥርዓት በየ ቤቱ ተሰሩ።ባል አልቦ ሴቶችና አባት አልቦ ህፃናትም ፍርሃትና ንዴት በተቀላቀለበት ስሜት የዕለቱን እንግዶች ሁኔታ ይታዘቡ ጀመር በሁኔታቸው ያልተደሰቱት ወታደሮችም አፈሙዝ ደግነው የሚፈልጉት እንዲ ፈፀምላቸው አዘዙ። ሽብረብ ብሎ ትዛዙን የተቀበለ ግን አልነበረም።

ይህም ይበልጥ ብስጭትን ወለደና የሃይል እርምጃን አስከተሎ በሰደፍ፣ ባፈሙዝና በዕርግጫ ሴቶች ተደበደቡ። ይህን ጭካኔ የተመለከቱት ህፃናት ተላቀሱ።በለቅሷቸው ያልተደሰቱት ወታደሮችም እንደ እናቶቻቸው ህፀናቱንም ባፈሙዝ እየጎሸሙ አስፈራርተው ፀጥ አሰኟቸው። አመሻሹ ላይም ከስምሪት የተመለሱት በጎችና ፍየሎች ወደ ጋጥ ከመግባታቸው በፊት የግፉ ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ ቀን ፈርዶባቸው ከፊሎቹ ታረዱ። ያች ዕለት ለዚያች መንደር የመስቅ ቀን ሁና ዋለችና አደረች።

እንዳይ መሽ የለም ብርሃንም ለጨለማ ቦታውን እየለቀቀ ሄደ። የምርጡ ዘር ኮርማዎችም ዐይኖቻቸው ባሩፉባቸው ሴቶች ላይ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ሲፈፀሙባቸው አደሩ። የወንዶቹ አገር በፍርሀት በፀጥታና በጨለማ ተወርሶ ብዙ ዲቃላዎችን ሲያፀንስ አደረ። በወያኔ ወታደሮች። ውርደት በምርኮ ያስቀመጣቸው ሴቶችም ውርደቱ በነርሱ ፈቃደኝነት የተፈፀመ ይመስል ባልፈፀሙት ሀጢአት አፍረው አንደኛዋ የሌላኛዋን ፊት ላለማየት ሁሉም እንደ ባህታዊ በየቤታቸው ራሳቸውን ዘግተው ዋሉ።

በዚህ መልክ ወር ሁለት ወር ብሎም ዘጠኝ ወር ተቆጠረ። የምጥ ቀንም ደረሶ የጀግና ሚስት የደመኛዋን ዲቃላ አምጣ ለመውለድ ዳግም ተንበረከከች። እንደ የወርቅ ውሃ ዓይነቶቹ ግን የባላቸውን ገዳይ ዲቃላ አምጦ ከመውለድ ሞትን መርጠው ገድለው ሞቱ።አንዳንዶችም ዲቃላውን ከእንግዴ ልጁ ጋር ጠቅልለው በመቅበር ቁጭታቸውን ተወጡ። ሆኖም ይህ ድርጊት ወደ ባለቀኖቹ ጆሮ ደርሶ ብዙዎቹ ገና በአራስ ቤታቸው እንዳሉ በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተከሰው ወደ ትግራይ ተወስደው አስከ ወዲያኛው አልተመለሱም። የነዚህ ግፉአን ልጆችም ወንዶቹ ያባቶቻቸውን ዕጣ ፈንታ ሲወርሱ ሴቶቹም እድሜ ላረጋዊ በርሄ እንደ ቀሪዎቹ የወልቃይት ሴቶች የምርጡ ዘር ኮርማ ቅምጦች ሆነዋል። የወልቃይት መሬት ይህንና ይህን መሰል ብዙ እጅግ ብዙ ዘግናኝ ገጠመኞችን ለታሪክ አስመዝግቧል። ዛሬ የወልቃይት ሴቶች ማስወረድ ሰለማይፈቀድላቸው የጠላቶቻቸውን ዲቃላዎች ተገድደው በማሳደግ ላይ የገኛሉ። እነዚህ ዲቃላዎችም ናቸው ነገ እነ አረጋዊ በርሄ ላቀዱት ሬፈረንደም (ውሳኔ-ህዝብ) ተስፋ የተጣለባቸው። ልጅ በአባቱ ይጠራል ነውና በነዚህ ዲቃላዎች ድምፅ ነው የወልቃየትና ለሙ የጎንደር መሬት ቋሚ የትግራይ መሬት እንዲሆን የታቀደው።

የሆነ ሆኖ ግን ጊዜ የኔ ነሽ ሲሏት የሌላ፣ የግሌም ሲላት የሁሉም፣ የማትለወጥ አድርገው ሲገምቷት ተለዋዋጭ፣ ሲያምኗትም የምትከዳ ክስተት ነች እንዳለው ደቡብ አፍረቃዊው ማርክ ማታቤን የዛሬው ቀን ለነገው መኖር ዋስትና ሰጪ አለ መሆኑ ባይዘነጋ ጥሩ ነው።ተጠቂው ወገንም ጊዜ በጣለበትን ዕዳ ይብላኝ ለአበዳሪ እንጂ እስከ ወለዱ ይከፈላል።እነ አረጋዊ በርሄ ግን ዛሬ ላይ ቆመው ነገን ላለማየት ተጨፍነው የትግራይ ህዝብ በዚህ አገዛዝ ተጠቃሚ አይደለም ማለት ይችላሉ። ሀቁ ግን የትግራይ ህዝብ ባገዛዙ ተጠቃሚ መሆኑን አይደብቅም። የወያኔ መንግስት ለራሱ ዘር ጥሩ መንግስት ነው።

የጥሩ መንግስት መስተዳድር መስፈርቱ የሚለካው ለሚገዛው ህዝብ በሚሰጠው የተሟላ የጤና፣ የትምህርት፣ የመገናኛ፣ የውሃ፣ የመብራትና የሥራ መስክ አቅርቦት ነው። እነዚህ አቅርቦቶችም ለትግራይ ህዝብ ግልጋሎት እየሰጡ አይደለም ብሎ ማመን ቢያንስ ሽፍጥ ነው።አገዛዙ የትግራይን ህዝብ አልጠቀመም ብለው ለማመን የሚፈልጉ ወገኖች አንደም ፈረንጆቹ እንደሚሉት ፖለቲካሊ ከሬክት መስለው ለመታየት የሚሹ ፖለቲከኞች አለያም እንደ አረጋዊ በርሄ ተጨፈኑና ለሞኛችሁ ባዮች ናቸው።እነዚህ ሰዎች በዛሬዋ ኢትዮጵያ የወባን በሽታ ወረርሽኝነት የሚክዱ፣ ወደ ህክምና ጣቢያዎች የሚሄዱ በሽተኞች የጓንት፣ የመርፌ፣ የፋሻና የአይዮዲን አቅርቦት ሳይቀር ከራሳቸው ከበሽተኞቹ እንጂ ከጤና ተቋሞቹ አቅርቦቱ የማይጠበቅ መሆኑን የማያምኑ ላገዛዙ የጥቅም ቅርበት ያላቸው ብቻ ናቸው።

የትግራይ ተወላጆች የተመቻቸላቸውን ሁኔታ ተጠቅመው በመንኛውም የአገሪቱ ግዛቶች እንደ ልባቸው ተዘዋውረው የመሥራት ነፃነት አላቸው። ሥራ ደግሞ ዳቦም ሀብትም ነው። ሃብትም ከበሬታን የጎናፅፋል። ሁሉም ባለው ያምራል እንዲሉ ያለው ጠግቦ ማድር ብቻ ሳይሆን የስልጣንም ባለቤት ነው። ለትግራይ ህዝብ ይህ ሁሉ አልተጓደለበትም። ዕድሜ ለነ አረጋዊ በርሄ ልጆቹ በተሟላ ትምህርት ቤት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየታነፁ ነው። ባንፃሩ የጨርቁ ዘር ልጆች ግን በትውልድ ገዳይ የትምህርት ሥርዓት በጅምላ የድንቁርና ምርኮ ሆነዋል። ዕድሜ ለወያኔ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ሁልም ልጆች ዕኩል ናቸው። አንዳንዶቹ ግን የበለጡ ዕኩል ሆነዋል።

በ1960ዎች መጨረሻ እነ አረጋዊ በርሄ ትግራይ ለትግራዊያን ብቻ ብለው ኢህአፓን ከትግራይ ካስወጡ በሁዋላ ትግራይ ለትግራዊያን የግል እንደሆነች ነች።ይልቁንም የግላቸውን የግል አድርገው የትግራይ ተወላጆች በመላዋ ኢትዮጵያ ተዝናንተው ሲኖሩ ጉራጌዎች ከአጋሮ፣ አማራዎች ከደቡብ፣ ከደቡብ መሥራቅና ከደቡብ ምዕራብ ግዛቶች በክልልህ እየተባሉ ከቀያቸው ሲፈናቀሉ አይስተዋልም። የደራ የደራው የንግድ ቦታም ከጉራጌው፣ ከአማራውና ከሌላው ዘውጌ እየተነጠቀ የሚሰጠው ለትግራይ ተወላጆች መሆኑ ፀሀይ የሞቀው ሃቅ ነው።በደርግ ዘመን የተወረሱ የከተማ ቦታዎችና ትርፍ ቤቶች በትግራይ ግዛቶች ለባለቤቶቻቸው ተመልሰዋል።

ከትግራይ ክልል ውጭ በሌሎች ቦታዎች የተወረሱት ግን ባገዛዙ ስር ወድቀው ሻጭ ወያኔ ገዥም የምርጡ ዘሮች ሲሆኑ ይስተዋላል።

ግማሽ ተላጭቶ ግማሽ ተቀብቶ የሆነ አገዛዝ መዳፉን ባሳረፈባት አገር ሁለት ዓይነት ያገዛዝ ፖሊሲ ተዘርግቶ ሁለት የመሬት ሁለት የትምህርት፣ ሁለት የጤና፣ ሁለት ያስተዳደር ፖሊሲዎች የሚተገበሩት ማንን ጎድቶ ማንን ለመጥቀም እንደሁ ማብራራት አይኖርብኝም። ታዲያ ይህ መድሎ የትግራይን ህዝብ በወየኔ አገዛዝ ተጠቃሚ አያደርገውምን? እነ አረጋዊ በርሄስ ይህንን ወርቃማ እድል ከትግራይ ህዝብ ነጥቀው ለቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሰጡት ታስቦ ነው በተቃዋሚው ጎራ እዲሰለፉ የሚታጩት? ጎበዝ እንድ ቦታ ላይ ቆም ብሎ ማሰብ ብልህነት ነው። ገብስ ነቀዝ በልቶ እስኪ ጨርሰው ራሱን አይከላከልም።እኛም ብዙ ጊዜ ገብስ ሆነን ቆይተናል። ቀደም በኢድሃቅ ራስ መንገሻ፤ ደረጀ ደሬሳ፤ ከ/ል ጎሹና አሰፋ ጫቦ?..ወዘተ ምርቃችንን እየሰበሩ አሽተው ቅመውናል። ዛሬ ደግሞ ለአረጋዊ በርሄ፤ ነገደ ጎበዜና መሰል ባንዳዎች የሰፌድ ቆሎ ሆነናል። መቼ ነው ገብስነታችን ቀርቶ ነቀዝን የሚያስደነግጥ አቋም የምንወስደው?